የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ — ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 35
ADDIS ABABA – 7th July, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፹፰ ዓ·ም·
ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶና ልማት ፈንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ . ገጽ ፪፻፷

## CONTENTS

Proclamation No. 45/1996
International Development Association Loan Agreement for financing the Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund Project Ratification Proclamation .................................................... Page 260

## አዋጅ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፹፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶና ልማት ፈንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· 80,800,000 (ሰማንያ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስ ገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶና ልማት ፈንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 45/1996

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, A Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of eighty million eight hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 80,800,000) for financing the Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund Project, was signed in Washington D.C., on the 15th day of May, 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of July, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing the Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund Project Ratification Proclamation No.45/ 1996."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ማይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር 2841 ኢ.ት.የብድር ስምምነት ነው ።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን 80,800,000 ኤስ.ዲ.አር. (ሰማንያ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement " means the Loan Agreement No. 2841 ET signed in Washington D.C. on the 15th day of May, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of eighty million eight hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 80,800,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of July, 1996.

Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE